# አቶ ክንፉ አሰፋ፣ ከመጠምጠም መማር ቢቀድም!

የጽሁፌ መነሻዉ አቶ ክንፉ አሰፋ (‘አቶ’፣ በተለምዶው መሠረት ነዉ፤ ካልፈለጉት ወይም ሌላ ቀዳማይ የስምዎ ቅጥል ካለዎት፣ ይቅርታ ስለማላዉቀዉ ነዉ) “ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ ጻፉ (እኛና አብዮቱ)” (ቀይ ቀለምና የቅንፉ ጭማሪ የእኔ) ብለዉ በሳይበሩ ዓለም የበተኑት የአሻሻጭነት ማስታዎቂያ ነዉ (<http://ecadforum.com/Amharic/archives/10463/>)።

አርዕስቱንና የመጀመሪያዉን አንቀጽ በማዬት ብቻ እንኳ “ኢሕአፓ ነዉ ወይንም ሳይሆን አይቀርም” ለምትሉ ወገኖች፤ መልሴ፣ አዎን። እኔ፣ እንደ ጅቡ “እንብላ ካላችሁ እንብላ፤ አንብላም ብትሉም እንብላ” እንዳለዉ - “ኢሕአፓ ነህ”፣ ብትሉኝ፤ አዎን ኢሕአፓ ነኝ፤ “አይደለህምም” ብትሉኝ፣ “ኢሕአፓ ነኝ” - አውቃችሁ ግቡበት እያልኩ ወደ ጉዳዬ ልግባ።

አቶ ክንፉ አሰፋ (የኢትዮጵያ ሜዲያ መድረክ ባለቤት መስለዉኛል፤ ካልሆኑ እታረማለሁ) በሳይበሩ ዓለም የበተኑትን የአሻሻጭነት ማስታዎቂያዎን ባዬሁ ጊዜ ባጋጣሚ እኔም ከአብዮቱ ታሪካችን ጋር በተያያዘ አንድ መጣጥፍ ቢጤ ለማህደሬ እያዘጋጀሁ ነበር። ማስታወቂያዎን አንብቤ እንደጨረስኩ አንደኛዉ ልቤ ዝም አትበል፤ “ለአቶ ክንፉማ መልስ መጻፍ አለብህ” እያለ እረፍት ነሳኝ። ቀደም ብዬ የጀመርኳትን ማስታዎሻዬን ሊያስጨርሰኝ አልቻለም።

የጀመርኳትን ማስታዎሻዬን ለጊዜዉ ዘጋሁ። ሌላ አዲስ ገፅ ከፈትኩ። እለቱ ማክሰኞ፣ ታኅሣስ 22 ቀን 2006 ዓ/ም፣ ሰዓቱ ደግሞ 8:15 ከተሣዓት ላይ ነበር። መክተቤን ጀመርኩ። “‘ሻምበል ፍቅረሥላሴ ወግደረስ ጻፉ’ እና ምን ይደረግ፣ አቶ ክንፉ አሰፋ?” ብዬ።

በመሀሉ እምሄድበት ጉዳይ ትዝ አለኝና፣ ከ 15 ደቂቃዎች በኋላ ይህንንም መጣጥፍ አቋረጥኩና ከቤቴ ወጣሁ - የቢሮ የሥራ ሰዓት እንዳያልፈኝ። በእግሬ ነበረና እምጓዘዉ፤ እምንገዴም ላይ ሌላኛዉ ልቤ (ልቦና፣ ቀልብ ልበለዉ ይሆን) “ርዕስህን ቀይር” አለኝ። ሁለት ልቦች ነዉ ያሉኝ። እናንተም እንደ እኔዉ ሁለት ልቦች አሏችሁ።

“ርዕስህን ቀይር” ያለኝ ልቤ፣ አይታይም፤ አይዳሰስም። እንደ አንደኛዉ ልቤ አራት ክፍሎችም የሉትም። ደም ቅዳ፣ ደም መልስ ቧንቧዎችንም አልፈጠረበት። ብቻ፣ ማዛባትን አያዉቅም። ልዋሽ ስል አትዋሽ ይለኛል። እማይሆን ነገር ልሥራ ሲከጅለኝም ተዉ! ይለኛል። ግን አንዳንድ ጊዜ ቀብ አልሰጠዉም ነበር። እናተም እንደ እኔዉ ትሆኑ ይሆናል። የልቤን ምክር ተቀበልኩ። ከሄድኩበት እንደተመልስኩም ርዕሴን ቀዬርኩ፤ “አቶ ክንፉ አሰፋ፣ ከመጠምጠም መማር ቢቀድም” አልኩት፤ እንደ ተመከርኩት።

መቸም ዘንድሮ፣ ሁሉም እዬተነሳ መጽሃፍ ማዉጣት ሆኗል። ደራሲዎቻችን መበርከታቸዉ ባልከፋም። ችግሩ፣ ለሽቀጥ ብቻ ተብሎ መሆኑ ነዉ እንጂ። ሃይ ባይ በሌለበት፣ ማንም እየተነሳ ልክ አላዋቂ ዶክተር ቦዳድሶ እንደ ለጣጠፈዉ ገላ፣ የእኛ ደረስኩ ባዮችም ቀራቅምቦዉን ሁሉ ከእዚህም ከእዚያም ለቃቅመዉና ለጣጥፈዉ ጻፍን ማለታቸዉ ነዉ። እሚገርመዉ ደግሞ የአሻሻጩ ማገብገብ። ለመርቁላቸዉ፣ ማስገደድ ነዉ። ጀማሪ ናቸዉ፣ ካልገዛችኋቸዉ ማስገደድ ነዉ። ደግሞም በጣም ፈጣጣዎች ናቸዉ፤ በጓደኛና በዘመድ አዝማድ ሁሉ ግዙን እያሉ መምጣታቸዉ። በሌለ ቤታችን የእኛ ኪስ ሊራቆት፤ የእነሱ ኪስ ሊያብጥ። እናንተም እንደ እኔዉ ተቸግራችኋል ይሆንን፣ ጎበዝ!?

ለእዚህ አባባሌ ሁለት የቅርብ ምሳሌዎችን ብቻ መስጠት ይበቃኛል - “የደም ዘመን” እና “ሞትና የኢትዮጵያ መሪዎች”። “ሞትና የኢትዮጵያ መሪዎች” ለቆርጦ ለጥፍ “ደራሲነን” ባዮች

ዓይነተኛ ምሳሌ ሲሆን፣ “የደም ዘመን” ደግሞ እጅ እግሩን ያጣ - አላዋቂ ዶክተር በልቶ (‘ል’ ይጥበቅ) በላልቶ የተዎዉ ገላ ይመስላል። ከቋንቋዉ፣ ካረፍተ-ነገሩ አሰካክ፣ ከሃሳቡ መሳከር ኸረ ስንቱ፤ ለማን አቤት ይባላል!? ደግሞ ደራሲው፣ “ደራሲ” ልበለዉ እንጂ፣ “ኢሕአፓ ነበርኩ” ሲል፤ ትንሽ እፍረት እንኳ እንዲህ ይጥፋ። እንደ እኔ ኢሕአፓ መሆን ቀርቶ፤ ኢሕአፓ አካል ገዝፎ ሲያልፍም ማዬቱን በጣም እጠራጠራለሁ።

ሁኔታዉ በደርግ ጊዜ “ወይ እሩጥ፤ ወይ ዝፈን” እሚባል የገንዘብ ማግኛ ዘዴ መጥቶ በጣም ተቸግረን የነበረበትን አጋጣሚ አስታዎሰኝ። ማንም እዬተነሳ ሲያናፋብን ለጆሮዎቻችን መጨነቅ ጀምረን ሁሉ ነበር። እነ አቶ ክንፉ አሰፋ በዚህስ ጊዜ ደርሳችሁበት ይሆናል። ዛሬስ “ወይ ወይን፤ ወይ ድረስ” ተብሎ ይሆንን? ያልሰማሁት ነገር፣ መጥኔ!።

“እኛና አብዮቱ” እንደ የአቶ ክንፉ አሰፋ የአሻሻጭነት ማስታዎቂያ አገላለጽ ከሆነ፣ እንደ አንዳንዶቹ “ደራሲ ናችሁ” በሉን ባዮች ቆርጦ ቀጥል ዓይነት አይመስልም። *“ጽሃፊው”፣ ይላሉ አቶ ክንፉ፣*

> *ጸሃፊው በድራማ መልክ በመጽሃፋቸው ካሰፈሩዋቸው እውነታዎችና ግለ-ሂሶች ውስጥ አንዳንዶቹን ለአንባቢያን ማካፈሉ አይከፋም።*

ብለዉ ያሰፈሯቸዉን አራት ነጥቦች አዬኋቸዉ። እነሱም፣

*”የፖለቲካ እሥረኞች በሙሉ እንዲፈቱ እሚለዉ ጥያቄ...፣ የነ ጀነራል ተፈሪ በንቲ ጉዳይን...፣ ሻምበል ፍቅረስላሴ ወግደረስ ስለ ልጅ ሚካኤል አስተዋይነት ሲያስታዉሱ...* እና *በወቅቱ ስለ ህዝቡ የእርስ በርስ መጨካከንና መወነጃጀል...”* (‘እና’ የእኔ ጭማሪ) ናቸዉ።

አስቀድሞ እንዳልኩት፣ ያዉ መጽሃፉን ለማሻሻጥ ስለሆነ፣ አቶ ክንፉ፣ የአባ ወግ-ደረስ ልጅ በእማያገባዉ ገብቶ በማቡካት ወገን እንደበደለ፣ ወላድን እንዳስለቀሰ፣ በመጨረሻም አገሪቱን ለገንጣይ እና አስገንጣይ ቡድኖች አስረክቦ ታሪኩ የታሪክ ትቢያ መልበሱን አምኖ እንደ ግለሰብ እንኳ ይቅርታ መጠዬቁን፤ ሌላዉ ቢቀር፣ በወያኔ ሚዲያ እንኳ ያለዉን ይቅርታ፣ በመጽሃፉ ማካተቱን አላመላከቱንም - እስቲ ጓግተን መጽሃፉን እንድንገዛዉ ሊሆን ይችል ይሆናልና ልተዎዉ።

ግን፣ በቅድሚያ ለአቶ ክንፉ አንድ ዓብይ ቁም ነገር ላስጨብጥ እወዳለሁ - ተቀበሉትም አልተቀበሉት።

አቶ ክንፉ፣ እርስዎና እርስዎን መሰሎች “አበላል እንደ ደርግ፤ አላባበስ እንደ ፍቅረ-ስላሴ ወግደረስ”ን እዬሰማችሁ ያደጋችሁ ኮበሌዎች፣ ስለ“አብዮታችን እና ስለፋሽስቱ ደርግ፣ ስለባንዶቹ” የታሪኩን ጅራት ብቻ ይዞ አንዳች ነገር ለማለት/ለመጻፍ ቆጠብ፤ ታሪኩን ጠልቆ ከማወቁ ላይ ቀደም፣ ቀደም ብታደርጉ አንድ የህክምና ዶክተር ለበሽተኛ ደንበኞቹ እንደ እሚያዝላቸዉ መድኃኒት (prescriptions) ሁሉ፤ እናንተም ምክሬን ሳትንቁ ብትቀበሉት ለፈዋሽነቱ እመኑኝ፣ ትድኑበታላችሁ። “ካላዋቂ ሳሚ...” ከመሆንም ለመጠበቅ (‘ጠ’ ይጥበቅ) - ፈተና ያለፈ መድህኒት ነዉ።

አቶ ክንፉ፣ ለምሳሌ፣ ያሻሻጭነት ማስታዎቂያዎ የሳተዉን እንዲህ አዬሁት። የወታደሩ ክፍል በታሪካችን ዉስጥ በጎም፣ ጥቁር ነጥብም አስመዝግቧል። “ጥሩዉ ታሪክ መኩሪያችን ነዉ” ብዬ ልለፈዉ፣ ይቅርታ። ጥቁሩ ነጥብ ካዔዉ መንግሥት ይጀምራል - የአባ ወግ-ደረስ ልጅ የወታደር ቤት ታሪክ ከተወጠነበት። እናም፣ በእዚህ ወታደረዊ ኃይል ነበረ ካዔዉ ጊዜ ጀምሮ

ስንታሰር፣ ስንፈታ፣ ባስለቃሽ ጭስ ስንታፈን የነበረዉ፣ በቆመጥ የተደለዝነዉ፣ በጥይት የተነደፍነዉ፣ በጉልበታም የዉኃ አሸንዳ ከመሬት የተደባለቅነዉ፣ በድንጋይ ፍልጥላጮች ላይ የእምብርክክ እንድንሄድ የተደረግነዉ፣ ከትምህርታችን የተጓጎልነዉ… በህይወት ያለን አንረሳዉም፤ አልረሳነዉምም። ካዜዉ መግሥትም በኋላም አገራችን በቁርጥ ቀን ልጆቿ ደም የታጠበችዉ፣ ዳር ድንበራችንን ለማስከበር እዬተዋደቀ የነበረዉን ኃይል እዬመረጠ በጥይት የቆላዉ ይህ የፋሽስቱ ደርግ ቡድን (ሻምበሉንም ጭምር) የወጣዉ ከእዚሁ የወታደር ቤት ነበር።

በመሆኑም፣ ቀደም ብዬ እንዳመለከትኩት የአባ ወግ-ደረስ ልጅ መጽሃፍ፣ የፋሽስቱ ደርግ ቡድን ከዚህ ዳራ ተነስቶ እስከ ግብአተ-መሬቱ ድረስ የፈጸመዉ "በጎ ሥራና በደል" ብሎ እሚያምነዉ፤ እናም፣ በተለይ የመጽሃፉ ደራሲ እንደ አንድ የፋሽስቱ ደርግ ቡድን አባልነቱ "ፈጸምኩት" እሚለዉ "በጎ ሥራና ክፉ አድራጎቱ" ምን ምን እንደ ነበረ መጽሃፉ ገበያ ላይ ሲዉል ገዝተን በማንበብ እምናዉቀዉ ቢሆንም፣ "ከአነጋገር ይፈረዳል፣ ከአያያዝ ይቀደዳል፤" እንደሚባለዉ፤ አቶ ክንፉ፣ አዉቀዉትም ይሁን ሳያዉቅት ባአሻሻጭነት ያወጡት ማስታወቂያዎ የአባ ወግ-ደርስ ልጅ ሁሉንም ነገር ወደ ሌሎቹ ለመወርወር የተዘጋጀ መጽሃፍ መሆኑን ከወዲሁ አሳብቆብዎታል፣ ይቅርታ፣ ከመጽሃፉ በጠቀሷቸዉ አረፍተ-ነገሮች የተሰበቀዉ የደረስኝ እንደ እዚያ ሆኖ ነዉና። እንመልከታቸዉም፤

> *…ተማሪዎችና የተለየ ዓላማ የነበራቸው የተማሩ ሰዎች የሰነዘሩትን መፈክር ብቻ ነበር ይዘን ንጉሡ ፊት የቀረብነው። …*

> *…የተለያየ ገንቢም ሆነ አፍራሽ ተልዕኮ ያላቸው ኃይሎች ተጽዕኖ እንደሚያሳድሩብን ያለማጤናችን፣ በየዋህነትና በቅንነት ብቻ እንደምንሠራ…*

*"…አፍራሽ ተልዕኮ ያላቸዉ…"*፣ አፍራሽ ተልዕኮ ያላቸዉ ብቻም ሳይሆን በተለያዩ ምክንያቶች ኢትዮጵያንና ሕዝቧን መበቀል እሚፈልጉ በዬትኛዉም ወገን ቢሆን እንደ እሚኖሩ/እንዳሉ፤ ኢትዮጵያንና ሕዝቧን ለመናድ ያገኙትን አጋጣሚ ሁሉ ለመጠቀም ከመሰለፍ ወደ ኋላ እማይሉ ግለሰቦች፣ ቡድኖች፣ ኃይሎችና አገሮች እንደ እሚኖሩ፣ እንዳሉም እሙን ነበር። ታይቷል። ዛሬም እዬታዬ ነዉ። በንብ ዘመን እንኳን ንቡ፣ ዝንቡ "ንብ ካልሆንሁ" ብሎ ማስቸገሩ እሚጠበቅ እኮ ነዉ። እናም፣ ዝንቡን አዉቆ፣ ለይቶ መከላከል እንጂ *"በየዋህነትና በቀናነት…"* ብቻ መሥራት ወንጀልን ከመሸከም አያድንም!። የራስን ስህተት ወደሌላዉ ለመወርወር መከጀል አጉል ድካም - "የአባዬን እከክ ወደ እማዬ ልክክ" ይሆንባችኋል እንጂማ ነዉ።

ወይ ደግሞ፣ "*የፖለቲካ እሥረኞች በሙሉ እንዲፈቱ የሚለው ጥያቄ እንደተነበበ ንጉሡ ጣልቃ ገብተው 'ለመሆኑ የፖለቲካ እሥረኞቹ እነማን ናቸው?' …*" ተብለዉ በአፄዉ ሲጠዬቁ ከመደንገጥ፣ እርስ በርስ ከመተያዬት፤ ገሌ መሌ እሚል ያልሆነ ምክንያት ከማብዛት…፣ "ፀሀዩ ንጉሣችን ሆይ! ተሳስተን ነዉ፤ የጠላት ወሬ ይዘን ነዉ፤ ይቅርታ ይደረግልን፤ ይማሩን፤ አይደግመንም" ብለዉ እንደ ሰለጠኑበት፣ የአፄዉን ጫማ ስመዉ መዉጣት እያለ። ለንስኃና ለመታመንም ሆነ ለማስደሰት የፈረደብንን እኛኑ መጥተዉ፣ በተለመደዉ ቆመጣቸዉ መቁመጥ፤ ማሰር፤ መግደል ይችሉ አልነበር። ሁሉ በእጃቸዉ፤ ሁሉ በደጃቸዉ፤ ማን ያግዳቸዉ ነበር። ያዉ፣ ቆይተዉ መግደላቸዉ አልቀረልን - ያዉም እስከ እነ አራጣዉ ሁሉ ነበር የከፈል ነዉ። እንዲያዉም፣ እንደ እዚያ አድርገዉልን ቢሆን ኖሮ፣ በኋላ ላይ የደረሰብን እልቂት እጅጉን በቀነሰ ነበር እሚል እምነት እስከ አሁን ድረስ አለኝ። ምን ያረጋል። አለፈ - የፈሰሰ ዉኃ እንደ አማይታፈሰዉ ሆኖ። ይህ ሁሉ የእዚያ የቂመኛው፣ የበቀለኛዉ፣ የ"ቆራጡና አብዮታዊ መሪ፣ መንግሥቱ" ብቻ ተንኮል ሁኖን ነዉን?። መጽሃፉ ግልጽ ካደረገዉ ጥሩ ነዉ።

ሌላዉ አማራጭ የነበረዉ ደግሞ፣ ተማሪዉም ሆነ ለዉጥ ፈላጊው ኃይል፣ “ከእዚህ በኋላ የደርግ ሥራ አይደለም፤ ሰፊ መሠረት ያለዉ (የወታደሩንም ቤት ተወካይ እሚያካትት ጭምር) ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋምና ሥልጣኑን አስረክባችሁ፣ በቃላችሁ መሠረት ወደ ጦር ሰፈራችሁ ተመለሱ” ብሎ ያቀረበዉን ጥያያቄ መቀብል ነበር። ለዉጥ ፈላጊዉ፣ ከሥልጣኑ ማማ ላይ እንደ ተንጠለጠላችሁ ቅሩ አላለም ነበር። እንዲያዉም፣ ያ ሁሉ ጥፋት የተፈጸመብን ሥልጣ እንድትለቁ ባደረግነዉ ትግል የተነሳ እኮ ነበር። አሁንም ድረስ፣ በውያኔ ጊዜ ለጥያቄዉ ህይወት እዬከፈለበት ነዉ። አብዛኛዉ የዛሬ “ተቃዋሚ በሉኝ” ባይ ከ 97ቱ ምርጫ ማለትም ካስራሰባትና ካስራስምንት ዓመታት በኋላ ነዉ የሽግግር መንግሥት ስለመቋቋም አጀንዳ ያደረገዉ - ልዩነታችን እንግዲህ ይህን ያህል መሆኑን ልብ ይሏል።

እንዲያዉም፣ “የእናንተ (የፋሽስቱ ደርግ ቡድን) የሥራ ድርሻ፣ ዓላማና ብቃት የአገር ዳር ድንበር መጠበቅ ነዉ” እያለ ነበር ለዉጥ ፈላጊዉ ያስተጋባዉ። ማንሰምቶ፤ ሁሉ ነገር በነበር ቀረ። “እነገሌን እሰሩ፣ ግደሉ፣ ባንዳን ፍቱ፤ መሬት ላራሹና የዕድገት በኅብረት...ዘመቻ አዉጁ፤ የከተማ ቦታና ትርፍ ቤት ዉረሱ...” ለዉጥ ፈላጊዉ ኃይል መች አለ።

ደግሞስ፣ አስራ ሰባት ዓመታት ሙሉ ሕዝብን እዬበደሉ፣ አገርን እዬናዱ፣ የእራስን ጓደኛንም እንኳ ሳይቀር በበነነ በተነነዉ እያጨዱ፣ የአንድነት ኃይሉን እያጠፉ፣ በኋላም አገርንና ሕዝብን ለከፋ ዘረኛ ቡድን - ገንጣይ-አስገንጣይ - አስረክቦ እዬኮበለሉና እዬተደበቁ ብሎ *“የዋህነትና ቀናነት”* አለ እንዴ? እዬቆዬን እማንሰማዉ ነገር የለም ለካ፣ ጎበዝ!። እናማ፣ ዉሻ በቀደደዉ ጅቡ ቢገባ፣ ጥፋቱ መች የጅቡ ሆነና።

እና ይህን ሁሉ ምን አመጣዉ? መጽሃፉ ሳታይ? የምትለዉ ጉዳይ በመጽሃፉ መልስ ተሰጥቶት ሊሆን ስለእሚችል ለምን ቸኮልክ የሚለኝ ካለ? መልሴ፣ እያልኩ ያለሁት በመጽሃፉ ላይ አይደለም። ሀቁን መጻፍ ወይም አለመጻፍ የጽሃፊዉ ጉዳይ ነዉ። እኔ ጉዳዩ ያለዉ ካሻሻጩ ላይ ነዉ። “ማንም ወንጀለኛ ሁሉ፣ ቀን ሰጥቶት በተነፈሰ ቁጥር የሌላዉ ማገብገብ ምን ቤት ነዉ?” ነዉ እያልኩ ያለሁት። ያጠያይቃል።

ሌላዉ ደግሞ፣ “በፋሽስቱ የደርግ ቡድን መካከል የዋሆች፣ ቀናዎች፣ የለዉጥ ፈላጊዉ ኃይል ደጋፊዎች አልነበሩም” እያልኩ እንዳልሆነ ይታወቅልኝ። ነበሩዋ። አንዳንዶቹም የመጽሃፉ ደራሲ በእሚያዉቀዉም መንገድ ሆነ በእማያዉቀዉ ሁኔታ ተበሉ። አንዳንዶቹም ሰልፋቸዉን አላሳመሩም። የቀሩት ደግሞ ሠሪ/አድራጊ ሳይሆኑ ተጎታች ብቻ ሆኑ። ሀቁ ይህ ነበር።

ከእዚህ በማስከተል ደግሞ፣ አቶ ክንፉ፣ ለምሳሌ፣ ለገበያ ማማሞቂያ ከጠቀሷቸዉ አራት ነጥቦች ዉስጥ በአራተኛዉ ነጥብ፣ ማለትም፣ *“በወቅቱ ስለ ህዝቡ የእርስ በርስ መጨካከንና መወነጃጀል ባሰፈሩት ክፍል ውስጥ እንዲህ የሚል ታሪክ እናገኛለን”* ያሉንን በዝርዝር ላዬዉ ፈቀድኩ። ይህ ለእኔ “ለቀባሪው አረዱት ነዉ” እሚሆነዉ - ያዉ፣ “ውሻ በቀደደዉ ጅቡ ገባ” ነዉ መልሴ። የአባ ወግ-ደረስ ልጅም “ተረስቶልኛል” ብሎ ካልሆነ በስተቀር ግጥም አድርጎ ያዉቀዋል። አዲስ እሚሆነዉ “አበላል እንደ ደርግ፤ አለባበስ እንደ ፍቅረሥላሴ ወግደረስ”ን እዬዘመሩ ላደጉት ብቻ እንጂማ ነዉ።

እኔማ፣ በአዬዉ ጊዜም ጀምሮ፣ “ለዲሞክራሲ፣ ለዜጎች እንደ ዜጋ እኩልነት፣ ለሀይማኖቶች፣ ለብሄር/ብሄረሰቦች እኩልነት፣ ለመሬት ላራሹ...” ለዉጥ ፈላጊዉ ስንጮህ፣ ከወታደሩ አፈና ደብቆ ያተረፈን፤ አጋልጦም የሰጠን አዉቃለሁ። “ምናባቱ፣ ይበለዉ፤ እኛ ካልገዛን ብለዉ ነዉ እንጂ፣ እኒህ ፀሀዩ ንጉሣችን ባስተማሩ ምን አደረጉ?” ይል የነበረዉን ግጥም አድርጌ አዉቃለሁ። ልብ ያድርጉ አቶ ክንፉ፤ በዚህም ወቅት ለዉጥ ፈላጊዉን እሚያሳድዱ የነበሩት

ወታደሮቹ ነብሩ። ጸሃፊዉም እኮ ወታደር ነብሩ። ይህን ለእርስዎና መሰሎችዎ ነዉ እምነግረዉ እንጂ፣ ለደራሲዉ መንገርማ፣ "ለአንበሳ መምተር" ስለእሚሆንብኝ አልቃጣዉም።

በፋሽስቱ ደርግ ጊዜም ቢሆን፣ "ጊዚያዊ ሕዝባዊ መንግሥት" እንዲቋቋም ለዉጥ ፈላጊዉ አበክሮ በመጠዬቁ ከፋሽስቱ ደርግና ከባንዶቹ አፈናና ግድያ ደብቆ ያተረፈንም ሆነ አጋልጦ የሰጠንም የሕዝባችንን አካል ጠንቅቄ አዉቃለሁ - ማንንም የዛሬ ነጋሪ አልሻም። ተከስቶ ለነበረዉ መወነጃጀል ምክንያቶቹ ተዘርዝረዉ እሚያልቁ ባይሆኑም ጥቂቶችን ላስታዉስ። አይደለም ሕዝቡን፣ አይደለም ጉረቤትን፣ ባል ሚስቱን፣ ሚስት ባሏን፣ አባት እና እናት ልጆቻቸዉን፣ ልጆቻቸዉ አባትና እናቶቻቸዉን፣ እህት ወንድሟን/ወንድሞቿን/እህቷን/እህቶቿን፣ ወንድም እህቱን/እህቶቹን/ወንድሙን/ወንድሞቹን (ልክ የውግደረስ ልጅ እንዳለዉ) እርስ-በእርስ እዲገላለጡ ያደረገ የፋሽስቱ ደርግና የባንዶች ጥምር ቡድን ነበር። የምን ወዴት ወዴት ወሰድ ነዉ። ሠራተኛ ባሠሪዉ ላይ፣ አሠሪዉ በሠራተኛዉ ላይ እንዲነሳ ያደረገ ይኸዉ አረመኔ ቡድን ነበር። አዳራሽ ሙሉ ሕዝብ በንቃት ስም ዘግቶ ካልተገላለጣችሁ አትወጡም እያለ በማሸበር፣ በውሸት እንዲጠቋቆሙ መንገድ እዬቀደደ ያስጨንቅ የነበረ ይኸዉ ጭራቅ ቡድን ነበር። ከዚህ ላይ ከማሳዘን አልፎ እሚያስቅ አንድ ምሳሌ ላምጣ።

እኔ በነበርኩበት አካባቢ፣ እንደ እዚሁ አዳራሽ ሙሉ ሕዝብ ተዘግቶ፣ በዉጭም በዘመነኞቹ እዬተጠበቀና በዉስጥም በባለጊዜዎቹ አለቆች ንቃት ከተሰጠዉ በኋላ እንደ ተለመደዉ "ካልተገላለጣችሁ/ካልተጠቋቆማችሁ አትወጡም" ሲባል፣ ሕዝበ-አዳሙ ሲቁነጠነጥ፣ ሰ.ን. የተባለ ሰዉ የተቀመጠበት ወንበር ሲፏቀቅ ከመቀመጫ የወጣ ድምጽ ዓይነት ማሰማት። "ማን ነዉ? እራስህን አጋልጥ? ወይም ያወቃችሁ አጋልጡ?" መባል። ሰ.ን. "እኔ የተቀመጥኩበት ወንበር ነዉ። ወዲህ እና ወዲያ ስል ነዉ 'ጥዝ' እሚል ድምፅ የወጣዉ" ብሎ እዬተርበደበደ እራሱን "አጋለጠ"። ወዲያዉኑ ካብዮታዊ ዘመቻ ቀርቦ "አብዮታዊ ስብሰባን በማደናቀፍ  በሚል ወንጀል (በእነሱ ቋንቋ) ስድስት ወር እስራት ትከናንቦ ወህኒ ቤት የገባ አዉቃለሁ። ይህ "ፈጣሪ በማዉጫዉ አትረፈዉ" የተባለዉ ፍርድ ዓይነት ነበር በውቅቱ። "አብዮታዊ ስብሰባን" እንኳን ያደናቀፈ፣ ለማደናቀፍ ያሰበ ፍርዱ ሌላ ነበር። ግፉ እኮ እጅግ እሚዘገንን ነበር፣ አቶ ክንፉ።

ሌላ የግፍ ምሳሌ ልጨምር፣ ፋሽስቱ የደርግ ቡድን እና ባንዶቹ ልጆቿን ሙጥጥ ያደረጉባት አንድ እናት ምን ብላ እንዳለቀሰች ይመልከቱልኝማ አደራዎን፣ አቶ ክንፉ፣

*መላኩ ተፈራ፣ የግዜር ታናሽ ወንድም፣*
*እባክህን አንዱን ልጅ እምኳ ተዉልኝ፣*
*ድግም አልበረከክም።*

ሌላዉ፣ ልጆቹ ተገለዉ ከበራፉ ላይ የተጣሉበት አባት አታልቅስ ተብሎ የተደበደበዉን በማስታዎስ (ይህ እኔ እኖርበት ከበበረዉ ቀበሌ ነዉ)፣ በጤነኛ ሞት (በቀይ ሽብር ያሆነ ለማለት ነዉ) ከሞተዉ የጉረቤት ልጅ ለቅሶ ላይ እንደ እሚከተለዉ ብሎ አስለቅሶ ነበር።

*አታልቅሱ ተብሎ ታዉጆ ነበረ፣*
*ታዲያ ድሃ ምን ይብጀዉ፣*
*ታላንጎራጎረ።*

እነዚህን እና የመሳሰሉት የያኔዉ የዝሕቡ ብሶት መግለጫ ስንኞች ገና እስካለም-ዓለሙ ድረስ ሲጮሁ ይኖራሉ እንጅማ - መች ቢረሱ።

በእዚያ ዘመን፣ መጠቆምም፣ ማሳሰርም፣ መግደልም፣ ማስገደልም… ያሾም፤ ያሽልም ነበር። በማን/በእነማን? በማንማ/ በእነማንማ፣ በእዚሁ ደራሲ ቡድንና በባንዶቹ እንጂማ ነበረ። የአባ ወግ-ደረስ ልጅ የሥራ ባልደረባ የነበረዉ ሌላዉ አረመኔ የአባ አራጋዉ ልጅ በማሳሰር የወረዳ አስተዳዳሪ ያደረገዉ የአብዮት ጥበቃ ሊቀመንበርና የወህኒ ቤት ፖሊስ የነበረ ሰዉ አዉቃለሁ። ደግሞ ይህንንም "ሕዝቡ እርስበርሱ ነዉ ያደረገዉ ብሎኝ ይሆንን" ደራሲዉ በመጽሃፉ፣ አቶ ክንፉ አሰፋ?

በከተማዉም በገጠሩም ፋሽስቱ ደርግና ባንዶቹ የማረክኸዉን መሣሪያ፣ በፍተሻም ያገኘኸዉ ሃብት ንብረት "ተባርኮልሃል" ስለተባለ፤ ሕዝባችን እርስበርሱ እንደተፋጀ የሩቅ ታሪካችን መች ሁኖ።

ቀሪ ሦስቱን ነጥቦችዎንም ቢሆን በእዚሁ መንገድ ባሳዬሁ ደስ ባለኝ ነበረ፤ ቦታ ማጣበብ ባይሆን ኑሮ።

ነገር ግን፣ መቸስ መጽሃፉ ለህትመት እስከ በቃ ድረስ፤ በግሌ ከአባ ወግ-ደርስ ልጅ መጽሃፍ እሚከተሉትን ዓብይ ነጥቦች ምላሽ እጠብቃለሁ።

1. አጼዉ፣ *"…ለመሆኑ የፖለቲካ እሥረኞቹ እነማን ናቸው? …"* ብለዉ ለጠዬቋችህ ጥያቄ መልስ እንደ ሌላችሁ ካወቃችሁና የሄዳችሁበትን ጉዳይ ከመለዎጥ ይልቅ በጉዳዩ እድትገፉበትና ተከታታይ እርምጃዎችን እንድትወስዱ በይበልጥ ይገፉ ወይም ይገፉ የነበሩ ማን ነዉ/እነማን ናቸዉ? የአባ ወግ-ደረስ ልጅስ ሚና ምን ነበር?
2. አፄዉ፣ ልጅ እንዳልካቸዉ መኮንን፣ ጽሃፌ ትዕዛዝ (ጠቅላይ ሚኒስትር) አክሊሉ ኃብቴና ሌሎች የአፄዉ ከፍተኛ ሹማምንት ለምን ተገደሉ? ዋናዉን ሚና የተጫወተዉ ማን ነበር? የመጽሃፉ ደራሲስ ሚና ምን ነበር?
3. ደርግ ጊዚያዊ መንግሥት ብሎ ለምን በእዚያዉ ረጋ? ለእዚህ ክህደት በዋናነት ተጠያቂዉ/ተጠያቂዎች ማን ነዉ/እነ ማን ናቸዉ? የአባ ወግ-ደረስ ልጂስ ሚና ምን ነበር?
4. የመጽሃፉ ደራሲ ቀይ ሽብሩን ተገቢ ነበር ብሎ ያምናል ወይ? ካመነ ለምን? አላስፈላጊ ነበር ካለስ ለምን? ቀይ ሽብር እንዲካሄድ በዋናነት ይገፉ የነበረ ማን ነዉ? ወይም እነማን ነበሩ? የአባ ወግ-ደረስ ልጅስ ሚና ከየትኛዉ ነበረ?
5. ደርግ/ኢሠፓ የአንድነት ኃይሎችን፣ ኢሕአፓን፣ ኢዲዩን… እዬወጋ ለምንድን ነዉ ተገንጣይ-አስገንጣይ ጋር ይደራደር የነበረው? ለእዚህ ማን ነዉ ወይም እነማን ናቸዉ ተጠያቂ/ተጠያቂዎች? የመጽሃፉ ደራሲስ ሚና ከየትኛዉ ወገን ነበር?
6. የእነ ኃሌ ፊዳ እና የብርሃነ-መስቀል፣ የባዕሉ ግርማና የከፍተኛ መኮንኖች ግድያ ላይ ዋናዉን ሚና የተጫዎቱት እነማን ነበሩ? የደራሲዉስ ሚና ምን ነበረ?
7. የመጽሃፉ ደራሲ እንደ ግለሰብ እና እንደ ቡድን ለተፈፀመዉ በደል ፍርድ ስጥ ቢባል ምን ይፈርዳል?

አቶ ክንፉ አሰፋ፣ የልጅ ሚካኤል እምሩ ስምን እዚህ ላይ ማንሳትዎ ታሪክ እንዴት እራሷን የእደጋገመችብን እንደ ሆነ አዕምሮዬ ያጫራቸዉ ሃሶብች ስላሉኝ፣ እነ እርሱኑ በድርሞዉም ቢሆን (ምክንያቱም ሁሉም ትልልቅ ጥራዞች እሚወጣቸው ጉዳዮች ናቸዉና) ጣል ጣል ባደርግስ አልኩ።

## የታሪክ ድግግሞሽ፣

- በ 1966 አፄዉ የለዉጥ ፈላጊዉን ኃይል ጥያቄ እሚያለዝብ የጥገና ለዉጥ ለማድረግ ዝግጁ አለመሆናቸዉ ስልጣኑ በፋሽስቱ የደርግ ቡድን እጅ እንዲወድቅ ማድረጋቸዉ፤ ደርግም ከአንድነት ኃይሉ ጋር ተባብሮ ገንጣይ-አስገንጥዮችን መከላከል ሲችል፣ ፈቃደኛ ባለመሆኑ በ 1983 ስልጣኑን ለገንጣይ-አስገንጣይ አሳልፎ መስጠቱ
- በ 1966 የተከሰተዉ የስልጣን ክፍተት በ 1983 መደገም፤ በሁለቱም አገራችንና ሕዝባችን ከጭቃዉ ወደ አረንቋዉ መግባት፤ ካፄዉ ወደ ፋሽስቱ ደርግ ቡድን፤ ከፋሽስቱ ደርግ ቡድን ወደ ወያኔ
- ለዉጥ ፈላጊዉ ኃይል በሁለቱም ጊዜ ቢሆን **የለዉጡ ባለቤት ለመሆን በሚያስችል ደረጃ ብቃት ያለዉ ሆኖ አለመገኘት**
- በሁለቱም ጊዜ፣ በ 1966 ዓ/ም እና በ 1983 ዓ/ም **የለዉጡን ዉጤት ነጣቂዎች በመሣሪያ የታገዙ ባለጡጫዎቹ እንጂ የእዉቀትና የአስተዳደር ብቃት ያልነበራቸዉ ኃይሎች መሆናቸዉ**
- ለሁለቱም ስልጣን ነጣቂዎች አደግዳጊ ምሁራንና ሆዳደር ቢሮክራቶች የጊዜ መግዣነት አገልጋይ መጋዣዎች መሆናቸዉ

  ከዚህ ላይ፣ የተከበሩ አርበኛና ደራሲ ሀዲስ ዓለማዬሁን እና ታዋቂዉን ፕሮፌሰር አስራት ወልደዬስን ሳላስታዉሳቸዉ ማለፍ አልፈቀድኩም - ደራሲ ሀዲስ ዓለማዬሁ በደርግ ጊዜ፣ ፕሮፌሰር አስራት ወልደዬስ በወያኔ። ደርግ ከልጅ ሚካኤል እምሩ በፊት ለጠቅላይ ሚኒስትርንነት ያጨዉና የለመነዉ ደራሲ ሀዲስ ዓለማዬሁን እንደ ነበር እሚዘነጋ አይደለም። ደርግን ማገልገል አልፈቀዱም፤ ሁለት ጊዜ አርበኛ ሁኖ ታሪክ ሠርቶ ማለፍን **ከተከበሩ አርበኛና ደራሲ ሀዲስ ዓለማዬሁ እንማር**። እንደዚሁም ሁሉ፣ የወያኔንን የሽግግር መንግሥት ለማቋቋም በተደረገዉ ጉባኤ ከተገኙት የወያኔ ታዳሚዎች መካከል ታዋቂዉ ፕሮፌሰር አስራት ወልደዬስ ብቻ ነበር ተቃዉሚቸዉን ያሰሙት። ስምን ይዞ አለመቀበር ማለት እንደ ሁለቱ አርበኞቻችን እንጂማ ነዉ። ምስጋና ለሁለቱም። በታሪካችን ሲዎሱ ይኖራሉ።
- የደርግም ሆነ የውያኔ ቁንጮዎች በማንነት ኪሳራ እሚሰቃዩ (identity crises sufferers) የሆኑ/የበሩ፣
  - ➢ መንግሥቱ፣ በነበረዉ የኋላ ቀር ባህላችን ኅብረተ-ሰባችን "አጥንተ-ሰባራና አጥንተ-ሰባራ ያልሆነ" እሚል ዘይቤ ነበረዉ። "አጥንተ-ሰባራ" ያልሆኑት፣ "ሰዉ" እሚባሉት ነበሩ፤ የታወቁም ስለነበረ ልተዎዉና "ሰዉ" አልነበሩም ወደ እሚባሉት ማለትም፣ በሥራቸዉ (ቀጥቃጭ፣ ሸማኔ፣ ፋቂ፣ መጫኛ ነካሽ...)፣ በእምነታቸዉ፣ በዘራቸዉ፣ በቋንቋቸው፣ በቀለማቸዉ (ጠቆር፣ ጠጉሩ ቁጥርጥር፣ ከንፈሮቹ ከበድ ያሉበትን ሰዉ ወፍጮ ላሽ ባሪያ...) በመባልና ዝቅ ተደርገዉ ይታዩ ስለነበር፣ "መንግሥቱም ከእነዚህ ኋላ ቀር ባህሎች አንዳቸዉ ተፅዕኖ ሳይኀዳ አልቀረም" ይባል የነበረዉ እዉነት ስለሆነ ይመስለኛል ያን ያህል ቂመኛና በቀለኛ የሆነበት ምክንያቱ።
  - ➢ መለስ፣ የመለሱማ ድርብ ነዉ አሉ ምክንያቱ፣ ቂመኛና በቀለኛ ለመሆን የበቃበቱ። በአንደኛው "የባንዳ ዉላጅ እዬተባለ ማደጉን" እንደ ምክንያት እሚያቀርቡ አሉ። ሁለተኛው ደግሞ፣ "አማራዉ ለትግሬዉ ንቀት አለዉ፣ የተለያዩ አንኳሳሽ ቅጥሎችን በትግሬዉ ላይ መለጠፍ ይወዳል..." የመሳሰሉትን በዐዕሮዉ ቋጥሮ ማደጉን እንዳስረጅነት እሚቀርበዉ ነዉ። "ወርቅ ሕዝብ፣ ጀግና ሕዝብ፣ እንኳንም ከእናንተ የተፈጠርን ሆንንና ገሌ መሌ" ቅርሻቱ ለዚህ ሳይሆን አልቀረም ማለት ነዉ።
  - ➢ ሁለቱም [መንግሥቱና መለስ፣ አምባገነኖች፣ ትዉልድ መታሪዎች (የቅርብ ጓደኞቻቸዉንና ባለሟሎቻቸዉን ሳይቀር ሙጥጥ ከማድረግ እማይመለሱ፤ ያደረጉም)]፣

> ፈሪዎች፣ ከሃዲዎች፣ ተክለሰዉነታቸዉን አግዛፊዎች… መሆናቸዉ እጅጉንም ከአንድ ወንዝ የተቀዱ አስመስሏቸዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምን እንዲህ ታሪክ እንደሚደጋገምበት ሚስጥሩ ከቶ ምን ይሆን? ወይስ ታሪክ ሁልጊዜ እንደዚህ ነዉ ማለት ነው? አያጠያይቅም ብላችሁ ነዉን፣ ጎበዝ!

እስቲ ይታያችሁ፣ የኢትዮጵያን ሕዝብ እኔ እንኳ እስከ እማዉቀዉ ድረስ (በእዚች ዕድሜዬ ማለቴ ነዉ)፣ እርሱ እዬተራበ ገዥዎቹን እሚቀልብ፤ እዬታረዘ እነሱኑ እሚያለብስ፣ እሚሸልም፤ ልጆቹን ሳያስተምር የእነሱን ልጆች እሚያስተምር፤ እርሱ በበሽታ እዬተሰቃዬና ባጭር እዬቀረ ለገዝዎቹ ጤናና እረዥም ዕድሜ እሚፀልይ፤ ሱባኤ እሚገባ… ነዉ። ታዲያ! ጥፋቱ ምኑ ላይ ይሆን፣ መከራዉ የበዛበቱ?።

ከቶ፣ ይህን ልማዱን ቢተዉ መፍትሄ ያገኝ ይሆን? "የሰይጣን ጆሮ ይደፈን"፣ እንዳያስብቅብኛና አኩራፊዎች እንዳይበዙ - "ጽድቅና ኩነኔ ኖሩም፣ አልኖሩም፤ ከክፋት፣ ደግነት ሳይሻል አይቀርም"ስ ተብሎ የል። ደግ መሆን ይመረጣል።

አቶ ክንፉ፣ በመቀጠልም፣ በሁለተኛነት ላስገነዝብዎ እምፈልገዉ፣ በእዚያ ወቅት፣ በያ! ትዉልድ የተነሱ ጥያቄዎችን ፋሽስቱ የደርግ ቡድንና ባንዶቹ ነጥቀዉ እንዳይሆን እንዳይሆን ማድረግ እንጂ፣ ጥያቂዎቹን እንዳልመለሱ፤ ጥያቄዎቹ ሳይበረዙ ሳይለዎጡ ዛሬንም ድረስ እዬተጠየቁ መሆኑ፣ ያ! ትዉልድ ለአገሩ፣ ለሕቡ ምንኛ የራቀ፣ የጠለቀ፣ የረቀቀ ራዕይ እንደነበረዉ፤ እንዳለዉም ልብ እንዲሉት ነዉ። በማታዉቁት ወይንም ማወቅ በማትፈልጉት ጉዳይ፣ ባለማወቅም ይሁን ወይንም ይሁነኝ ብላችሁ እያደረጋችሁት ያለዉ ትግል አይሉት ነገር እዬበዛ መጥቷል። እዬተስተዋለለ ቢሆን ነዉ ለሁላችንም እሚበጀዉ። ጊዜዬያችንን በወያኔ ላይ እናዉለዉ። ገና ሜዳዉ አመችቷል ተብሎ እንደፈለጉ መጋለብ ደግም አይደል። ልጓም ይበጅለት - "መከበር በከንፈር" ነዉና እንዲሉ።

እኔ፣ የወደቀን፣ የሞተን፣ የድሮዉ ሕዝብ በዳይና አገር ናጅን ከምቃብር ቀስቅሶ ወያኔን ለመተካት እዬተደረገ መፍጨርጨር በዋና ጠላት ላይ እንዳናተኩር እሚያደርግ ስለለሆነ ከዋናዉ ጠላት፣ ከወያኔ ተርታ አሰልፈን እንታገላቸዉ፤ እንፋለመዋለን ባይ ነኝ፤ እንዲያዉቁልኝ። እናም፣ **ከመጠምጠም መማር ይቅደም**! ስላልኩ እንደ ክብረነክ ባይቆጠርብኝ፣ አቶ ክንፉ አሰፋ። በቃኝ።

ግፈፍኛዉ፣ ወንጀለኛዉ ሁሉ ለፈፀመዉ ግፍና ወንጀል እሚጠዬቅበት ቀን እሩቅ አይደለም። ኢትዮጵያ በነጻነት፣ በሰላም፣ በእኩልነት በተድላና በደስታ ለዘላለም ትኑር!

ቸር ያምጣ!

ጃንተከል ተኳለ
ታኅሣስ 23 ቀን 2006 ዓ/ም፣ 05:35 ከተሣዓት በፊት